BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## How do I get to...?

## ወደ. . . የምሄደው እንዴት ነው?

*This is not a word-for-word transcript*

ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊተዋቸው የማይቻላቸውን የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation በደህና መጡ። ምህረትእባላለሁ። በዚህ ክፍል በሚኖሩበት ከተማ ውስጥ ወደተለያዩ ቦታዎች እንዴት መሄዴ እንደሚቻል መጠየቅን ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች ወደመሸጫ መደብር እንዴት መሄድ እንደሚቻል ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

***Phil***
*How do I get to the supermarket?*

***Sam***
*Turn left, go straight on, turn right, it's on Queen Street.*

***Phil***
*Thanks!*

ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን። የመጀመሪያው ተናጋሪ ወደ 'መሸጫ መደብር' 'supermarket' እንዴት መሄድ እንደሚቻል ነው የጠየቀው። የተጠቀመው የመጠየቂያ መንገድ 'ወደ . . . እንዴት መሄድ እችላለሁ' 'How do I get to…?' የሚለውን ነው፤ ከዚያም 'the supermarket' የሚለውን ሐረግ አከሎበታል። ያዳምጡና ሐረጉን ደግመው ይበሉ።

*How do I get to the supermarket?*

ከዚያም ሁለተኛዋ ተናጋሪ አቅጣጫ ሰጥታዋለች፤ በመጀመሪያ 'ወደግራ እንዲታጠፍ' ነው የነገረችው። ከዚያም 'ቀጥ ብሎ መሄድ' እንዳለበት 'go straight on' ነግራዋለች። በመጨረሻም 'turn right' 'ወደቀኝ ታጠፍ' ብላዋለች። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*Turn left.*
*Go straight on.*
*Turn right.*

ከዚያም 'የሚገኘው በኩዊን ጎዳና ላይ ነው' 'It's on Queen Street' ስትል ነግራዋለች። 'የሚገኘው' 'It's on…' ካለች በኋላ የጎዳናውን ስም ጨምራለች። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*It's on Queen Street.*

የመጀመሪያው ተናጋሪ ለተደረገለት ትብብር 'አመሰግናለሁ!' 'Thanks!' ብሏል። ሐረጉን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።


© British Broadcasting Corporation 2018

*Thanks!*

በጣም ጥሩ፤ አሁን የተለያዩ ሰዎች አቅጣጫ ሲጠያየቁ ያዳምጡና እርስዎ ያሉትን ያነፃፅሩ።
ፒት ወደ 'ባንክ' 'bank' መሄድ ይፈልጋል።

*How do I get to the bank?*

*Turn right, go straight on, turn left, it's on Perth Road.*

*Thanks!*

እሺ፥ አሁን ደግመን እንሞክር። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገራቱን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ይሰሟቸዋል።

*How do I get to the supermarket?*
*How do I get to the supermarket?*

*Turn left.*
*Turn left.*

*Go straight on.*
*Go straight on.*

*Turn right.*
*Turn right.*

*It's on Queen Street.*
*It's on Queen Street.*

*Thanks!*
*Thanks!*

በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱት እንመልከት። አረፍተ ነገራቱን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይናገሩ።

*ወደመደብሩ የምሄደው እንዴት ነው?*
*How do I get to the supermarket?*

*ወደግራ ታጠፍ።*
*Turn left.*

*ቀጥ ብለህ ሂድ*
*Go straight on.*


© *British Broadcasting Corporation 2018*

*ወደቀኝ ታጠፍ።*
*Turn right.*

*የሚገኘው በኩይንስ ጎዳና ላይ ነው።*
*It’s on Queen Street.*

*አመሰግናለሁ።*
*Thanks!*

በጣም ጥሩ፤ እሺ አሁን በእንግሊዝኛ እንዴት አቅጣጫ መናገር እና መጠየቅ እንደሚቻል አውቀዋል። ለመጀመሪያው ተናጋሪ ምላሽ በመስጠት፥ አቅጣጫ እየጠየቁ ልምምድ ያድርጉ።

*How do I get to the supermarket?*
*Thanks!*

በጣም ጥሩ፤ አሁን መልስዎን ለማመሳከር ጠቅላላውን ውይይት እንደገና ያዳምጡ።

***Phil***
*How do I get to the supermarket?*

***Sam***
*Turn left, go straight on, turn right, it’s on Queen Street.*

***Phil***
*Thanks!*

በጣም ጥሩ። አሁን በእንግሊዝኛ በሚኖሩበት ከተማ አቅጣጫ መጠየቅ እና መናገር ይችላሉ። የተማሩትን መለማምድን ያስታውሱ። ጓደኛ ይፈልጉና ስማችሁን መጠየቅና መናገርን ይለማመዱ። ለተጨማሪ የEssential English Conversation ዝግጅቶች በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። ደህና ይሁኑ!


*© British Broadcasting Corporation 2018*